**የመጽሃፍ ግምገማ**

**"እኛና አብዮቱ"**

**የታተመበት ታህሳስ 2006**

**ደራሲ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግ ደረስ ገጾች - 450**

**አሳታሚና አርታኢ -ጸሃይ አሳታሚ**

---

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ጉዳይ በርከት ያሉ መጽሃፍት በቅርቡ ለአንባብያን ቀርበዋል። ይህ ሊበረታታና እሰየዉ ሊባል የሚገባ ጅምር ነዉ። የደራሲዉ የመጀመርያ መጽሃፍ ከዚሁ ተራ የሚመደብ ነዉ። ታሪክን፤ በተለይ ባለሙያ ያልሆኑ ታሪከኞች ሲጽፉ ሊከተሏቸዉ የሚገቡ አበይት መመሪያዎች መኖር ይኖርባቸዋል። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸዉ።

1. ለሚቀርቡ ክሶችና ሃቅ ተብየዎች፤ ማስረጃ ማቅረብ። ይህ ማስረጃ ባለሙያ ታሪከኞች በግርጌ ማስታወሻና በመሳሰሉት መንገዶች ዋቢ እየጠቀሱ አሳማኝነታቸዉን ለአንባብያን የሚያቀርቡበት መንገድ ነዉ። አንዳንድ የስነጽሁፍ ዘርፎች፤ ለምሳሌ ግለታሪክ ይህን ህግ ብዙ አይከተሉም። አንድ ሰዉ ስለራሱ ታሪክ ሲጽፍ፤ በተቻለ መጠን ሌሎች የሚጋሩት ታሪክ ከሆነ አመላካች መስጠት ቢጠበቅበትም፤ በግርጌ ማስታወሻ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይጠበቅም። ታሪክ መጻፍ ግን ከዚህ የተለየ ነዉ።

2. ታሪኩ ስለራስ ፖለቲካ ድርጅት፤ ወይም ማህበር ወገንተኝነትን ያካተተ ከሆነ፤ የራስ ድርጅትን አሳብጦ፤ ሌሎችን አንኳሶ፤ ስለራስ ድርጅት ገመና ወይም ድክመት ሳያነሱ፤ ሌሎችን ብቻ ያዉም ያለምንም ማስረጃ ማሳነስና ማጥቆር ተአማኒነትን በእጅጉ ይቀንሳል።

3. ታሪኩ የተጻፈዉ፤ እንዲያዉ በድፍረትና አይንን በጨዉ ታጥቦ፤ አገር ያወቀዉን፤ ጽሃይ የሞቀዉን ሃቅ ሽምጥጦ ለመካድና አዲስ የዉሸት ታሪክ በቦታዉ ለማቆም ከሆነ ትዝብትን ከማትረፍ ዉጭ፤ ዉሸት ሲደጋገም ዉነት ይመስላል ቢባልም፤ እዉነትና ንጋት እያደረ ይገልጣል የሚለዉን ማሰሪያ አባባል ማጤን ያስፈልጋል።

የሻምባል ፍቅረስላሴ መጽሃፍ እነዚህን መመሪያዎች ከቁብ የቆጠረና ከግምት ያስገባ አይመስልም። ይህንኑ በማስረጃ ከመጽሀፉ እየጠቀስን እንመለከታለን። በተጨማሪም፤ ደራሲዉ የደርጉ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩና ኢሰፓ ይባል የነበረዉም ፓርቲ ባለስልጣን የነበሩ ናቸዉ። ደርጉ ተቃዋሚዎች እንደነበሩትም የታወቀ ነዉ። መድብለ ፓርቲ በሚሰራባቸዉ አገሮችም ይሁን፤ በአንድ አምባገነን ፓርቲ ስር በወደቁ አገሮች፤ አብዛኛዉን ጊዜ ህጋዊ ወይም ህቡአዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይኖራሉ። በዴሞክራሲያዊ አገዛዝ በሚተዳደሩ አገሮች ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደ ጠላት አይታዩም፤ እነሱን ለመደምሰስ ወይም ለማኮላሸት ገዥዉ ፓርቲ አያዉክም። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉን ሁኔታ ከዚህ አንጻር ስናይ፤ ትናንት የሻምበል ፍቅረስላሴ ኢሰፓ ሲያደርግ ከነበረዉ ብዙ የተለየ አይደለም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያኔም ጠላት ነበሩ፡ ዛሬም ናቸዉ። ወከባ እንዳይገጥማቸዉና በሰላም እንዲኖሩ ገዥ ፓርቲዉን "አሜን፤ አንተ ያልከዉ ብቻ""የምን አማራጭ አሳብ - ገዝዉ ፓርቲዉ ያመነጨዉን ብቻ አስፈጻሚ እንሆናለን" ብሎ ተቃዋሚ ሳይሆኑ ተለጣፊ መሆን ነዉ።

ኢሰፓ ከተፈረካከሰ ሩብ ምእተ አመት በኋላ እንኳን፤ ሻምበል ፍቅረስላሴ ባንድ አገር የተቃዋሚ ፓርቲን ሚና የተረዱ አይመስልም። በዚህ ሩብ ምእተ አመት በአለም ዉስጥ ብዙ ዴሞክራሲያዊ ለዉጦች ተደርገዋል። በርግጥ ደራሲዉ እስር ቤት ዉስጥ ነበሩ። ሆኖም ይህ ጊዜ ያለፈዉን ፖለቲካና ስህተቱንና ጥንካሬዉን፤ ወደኋላ ተመልሰዉ በእርጋታ ተመልክተዉ ሚዛናዊ አስተያየት ላይ ሊያደርሳቸዉ የቻለ አይመስልም።

ታሪክ ራሷን እየደጋገመች፤ ስለ ኢህአፓ ሲተርቱ "ስልጣን ለኔ ይገባኛል ብሎ እዉከት ፈጠረ" ይሉናል (ገጽ 223). የዛሬዉ መንግስት ስለተቃዋሚዎች የሚለዉ ይህንኑ ነዉ። ምናልባት "እዉከት" ሳይሆን "የከተማ ነዉጥ " የሚለዉ

ነዉ የሚለያያቸዉ። ይህ ደግሞ በነሲብ የመጣ ሳይሆን አምባገነኖች ሁሉ የሚከተሉት የማያዛልቅ የአቀበት መንገድ ነዉ። መነሻቸዉ "ዴሞክራታይዜሽን፤ መድበለ ፓርቲ፤ ሰብአዊ መብቶች፤ ወዘተ ገደል ይግቡ;፡ እኛ ስልጣን ላይ ብቻ እንቆይ" ነዉ። አስከትለዉም "ጠላት" ያሏቸዉን ተቃዋሚዎች ጥላሸት መቀባት ነዉ። የህዝብ መገናኛ መሳሪያዎች የፕሮፓጋንዳና የቅስቀሳ መሳሪያዎቻቸዉ ይሆናሉ፤ ተቃዋሚዎቻቸዉን ያስራሉ፤ ይገድላሉ።

ከዚህ ሁሉ አመታት በኋላ ደራሲዉ፤ የሰለቹና ማስረጃ የሌላቸዉን ክሶች እንደሚከተለዉ በኢህ አፓ ላይ ይጭናሉ።

● በመሬት አዋጁ ቤተሰቦቻቸዉ የተጎዱባቸዉ አይናቸዉን ጨፍነዉ የ ኢህ አፓ አባል ሆኑ ።- ገጽ 184

2

● ኢህ አፓ ገንዘብ እየሰጠና እያስገደደ አባላቱን መለመለ -ገጽ 247

● መስከረም 14 የአየር መንገድ ሰራተኞች ለመብታቸዉ መከበር ከመስሪያ ቤታቸዉ ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርጉ ደርግ 6 ሰዎች ገደለ፤ ሆኖም የመጀመሪያዋን ጥይት የተኮሱ ሰራተኞች ናቸዉ -ገጽ 251

● ኢህ አፓ ፋብሪካ አበላሽቷል፤ ኢቃጥሏል -ገጽ 253

● ሴቶች ዘማቾችን በጎረቤት አገር እያሸረሞጠ (ገላቸዉን እየሸጡ) የተገኘዉን ገንዘብ ለጸረ-ህዝብ ንግድ አዉለዉታል -ገጽ 257

● የሶማልያ ጦር ኢህኢፓን አስከትሎ ህዝቡን በመጨፍጨፍ ወደ ማህል አገር ገሰገሰ (ገጽ 340) ኢትዮጵያን እንዲወጉ ከሶማልያ ጋር ስምምነት ካደረጉ ድርጅቶች ኢህ አፓ አንዱ ነዉ (ገጽ 363)

● ኢህአፓ በስሜት ብቻ ይገፉ የነበሩ ወጣቶችን መልምሎ ወደ ሶሪያ ለስልጠና ለመላክ ችግር አልነበረዉም (ገጽ 353)።[እነዚህ በአፍላ ወጣትነታቸዉ የገበሬዉ ብሶትና ችግር እረፍት ነስቷቸዉ የራሳቸዉን ምቾትና ትምህርት ትተዉ፤ ደራሲዉ በወታደርነት ሙያ የራሳቸዉን እድገት ብቻ በሚያሳድዱበት ጊዜ፤ በረሃ የገቡትን አገር ወዳዶች ማራከስ ለታዛቢ ምን ይመስላል?]

እነዚህን አንዳንዶቹ ግብረገብነት የጎደላቸዉ ጸያፍ ክሶች ያለ ምንም ማስረጃ ከደፈደፉ በኋላ፤ ወደ ሌሎቹ ቀድሞ አጋሮቻቸዉ፤ በኋላ ግን ጸበኞቻቸዉ ወደሆኑት ግራ ዘመም ድርጅቶ ያልፉና ስም ይለጥፉላቸዋል - "የመኢሶን ኪሳራ" "ከመነሻዉም ያላማረበት ኢጭአት" "የወዝ ሊግ ከባድ ስህተትና ዉድቀት" "ታይቶ የጠፋዉ ማሌሪድ" እያሉ በስልጣን ላይ እንዲቆዩ ያገዟቸዉን የሰደድ ፓርቲ ተቃናቃኞች ሁሉ ያራክሳሉ።

የደርግ መንግስት በተለይም አምባገኑ መንግስቱ ሃይለማርያምና በዝምታና በአሽከርነት አስፈጻሚዎቹ በስልጣን ብቻ ለመቆየት ያችን አገር መቀመቅ እንደከተቷት፤ ተብሎ ተብሎ ያበቃለት ነዉ። ዛሬ ታዲያ ይቅርታ እንደመጠየቅና ሁሉም የድርሻዉን እንዲያነሳ የበኩላቸዉን እንደማገዝ፤ ቀደም ብሎ መንግስቱ አሁን ደግሞ ደራሲዉ በክፍት ቁስል ላይ ጨዉ መነስነሱን ተያይዘዉታል።

የደርግ ስርአት ያገሪቱን ችግሮች ለመፍታት ህዝባዊ መንግስት በማቋቋም ወይም እንዲቋቋም በማመቻቸት ሊያግዝ ይችል ነበር። ግን የስልጣን ጥም ያዞረዉ መንግስቱና ሊናገሩት እንኳን የሚፈሩት አሽከሮቹ ለዚህ ማእረግ አገሪቷን ሊያበቋት አልቻሉም። መንግስቱ ሃይለማርያም ራሱ እንዳመነዉ ወደ ስልጣን እንደመጡ ባስቀመጧቸዉ የሃሳብ መስጫ ሳጥኖች ዉስጥ ካገኙት ሃሳቦች ዉስጥ 60% የሚሆነዉ የህዝባዊ መንግስት መመስረትን የጠየቀ ነበር (ትግላችን ገጽ 164)። በኋላም የብሄራዊ አማካሪ ድርጅት መስርቶ፡ አማካሪዎቹ አዎንታዊ ስራዎች እየሰሩ እያሉ (ለምሳሌ አገሪቱ የምታከብራቸዉን በአሎች በአዲስ መልክ ማዋቀርና የሰራተኛ አዋጅ መንደፍ)፤ ህገመንግስት ወደማርቀቅና ወደህዝባዊ መንግስት ስርአት ሊጓዙ ይችላሉ በሚል ፍርሃት ጉባኤዉን አዳክሞ የተወሰኑ አባላትን በሹመት እያሰናበተ በትኖታል። ቀጥሎም ልጅ ሚካኤል እምሩን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገዉ ሾመዉ፤ ወይ አያሰሩት

ወይ አይሰሩ፤ አላነቃንቅ ብለዉት ከሃላፊነቱ እንደተነሳ የታየ ነዉ።

በዚህ ብቻም አላበቃም። እነ መቶ አለቃ አለማየሁ ሃይሌ ደርጉ በዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዲሰራ ያወጡት ረቂቅ የመንግስቱን ስልጣንና አምባገነንነት -በኋላም አገሪቱ እንድትፈርስና አሁን ላለችበት ሁኔታ ያበቃዉን ብልሹ አስተዳድር -ለማሻሻል ያደረጉትን ጥረት ደራሲዉ የማሻሻያ ሃሳቡ "የኢህ አፓ ስራ ነዉ" በማለት ብቻ፡ ጉዳዩን ከደሞክራሲና ከ አገሪቱ መጻኢ እድል አንጻር ማየት ተስኖአቸዉ፤ ዛሬ እንኳን አለቃቸዉ መንግስቱ ሃይለማርያም አገሪቷን አፍርሶ ሽሽቶ ካመለጠ በኋላ ወደ ኋላ አይተዉ "ያ መሻሻል ቢደረግ ኖሮ..." ብለዉ ለማሰብ የቻሉ አይመስልም። ይህ እንግዲህ ኢትዮጵያ ያመለጣት አንዱ እድል ነበር።

ሁለተኛዉና ተያያዥ እድል የደርጉ ሊቀመንበር ጀ/ል ተፈሪ በንቲ በ 1969 በወቅቱ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ እንዲተባበሩ በመስቀል አደባባይ ንግግራቸዉ ሲጠቅሱ፤ መንግስቱና አሽከሮቹ ተቀባይነት እንደሌለዉና እንዲያዉም "ከ ኢህ አፓ ጋር እርቅ ሳይሆን ትጥቅ ነዉ መፍትሄዉ" ብለዉ እንደፎከሩ ደራሲዉ የነገሩን ነዉ (ገጽ 318)። ጀ/ል ተፈሪ በንቲ የተገደሉበት ጥፋት ምንድን ነዉ? ለዚያዉም ባልተረጋገጠ የኢህ አፓ ደጋፊ ናቸዉ በሚል "ታላቅ ወንጀል"። በምንም መንገድ ስልጣኑ ከሚወሰድ እች አገር መቀመቅ ብትገባ ግድ የሌለዉ መንግስቱና አሽከሮቹ ዛሬ ላለንበት ሁኔታ ተጠያቂነታቸዉን ሊረሱት ከቶ አይገባም።

ደራሲዉ መንግስቱ ሃይለማርያም ምን አይነት መሰሪና ራስ ወዳድ መሪ እንደሆነ አጥተዉት አይደለም። ግን መኖርና በስልጣን መቆየት የፈለጉ ይመስላሉ። መንግስቱን የተቃወሙ ሁሉ የደረሰባቸዉን አይተዋል። ሲሳይ፤ አጥናፉ፤ አማን፤ ተፈሪ...አለማየሁ፤ ሞገስ...ወዘተ. ስለመንግስቱ እንዲህ ይላሉ "አንድ ግለሰብ ለመቃወም ወይም የተለየ አስተያየት ለመስጠት ሲሞክር ከባድ ቅጣት እንደሚደርስበት ስለሚታወቅ በግልጽ ተቃዉሞ ያሰማ አልነበረም (ገጽ 150)። "ሻለቃ መንግስቱ ፍላጎታቸዉን የሚጻረር አስተያየት በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ ይከፋቸዋል። ፊታቸዉን በማኮሳተር ሳያዉቁት ከንፈራቸዉን ይነክሳሉ። ጉንጫቸዉም ይንቀጠቀጣል። አቋማቸዉን የሚያጠናክር አስተያየት ሲሰነዘር ግን ይፈካሉ። ትክክል ነዉ! በማለት ያስፋፉና ይደግሙታል"(ገጽ 174)። አምባገነኑ መንግስቱ ሃይለ ማርያም የሚመራዉ ስብሰባ እንኳን እሱ እንደፈለገዉ ካልሄደ አቋርጦ አኩርፎ ጥሎ ወጥቶ ወደቢሮዉ ይሄድና ተለምኖ፤ተለምኖ ይመለሳል (ገጽ 189)።

ታዲያ ይህንን አምባገነን በመቃወም ኢህአፓ ባደረገዉ ትግል እንደመመስገን ይወቀሳል? በተቃዉሞ ትግሉ ኢህአፓ በሰራቸዉ በማስረጃ ተደጋፊነት ባላቸዉ ስህተቶቹ መዉቀስ የእናት ነዉ። ደራሲዉ ግን ይህን ሁሉ በመንግስቱ ላይ እየመሰከሩ የሱንና የሳቸዉን ጥፋት ጭርሶ አለማየታቸዉ አስገራሚ ነዉ። ጓዶቻቸዉ እነ ሻለቃ ወልደማርያም ሃይሌን፤ መቶ አለቃ ድንቁ ግሩምን፤ ሻለቃ ጌታቸዉ 3

አግዴን፤ የሰደድ አባል ሆነዉ የወዝ ሊግ አባልም ጭምር መሆናቸዉን ለመንግስቱ ስለነገሩ ብቻ (ሰደድና ወዝ ልዩነት ስላልነበራቸዉ) "እንዴት ይሆናል?" በማለት በእብሪት ሲገድላቸዉ ያለ ተቃዉሞ አብረዉ የተጓዙ ደራሲ ናቸዉ። 60ዎቹ የቀድሞ መንግስት ባለስልጣኖችም ሲገደሉ እንደዚሁ ደራሲዉ ካአጫፋሪነት ሚና ያለፈ፤ እንደ ጓዳቸዉ ሻለቃ ብርሃኑ ባይህ እንኳን "በህግ የተያዘ ጉዳይ ለምን በህግ አያልቅም?" (ገጽ 147) ብለዉ መንግስቱ ሃይለማርያምን ለመቃወም ሳይሆን፤ ለመጠየቅ እንኳን ድፍረቱ አልነበራቸዉም። በነገራችን ላይ፤ መንግስቱ ሃይለማርያም ለ60ዎቹ መገደል ወቀሳዉን በንኡስ ደርጎች ተገፍተን ነዉ በማለት መቼም ሃላፊነት ለመቀበል ወኔ ስለሌለዉ እነሱ ላይ ያላክካል (ትግላችን ገጽ 219)፤ ደራሲዉ ባይሆን ሃላፊነቱ የሁላችንም ነዉ ይላሉ። ወላድ በድባብ ትሂድ እንጂ የቀደሙትን የኢህአፓ አርበኞች የተቃዉሞ ፋና በመከተል፤ ዛሬም "እምቢ ዝም አንልም፤ አሽከር አንሆንም፤ ስላገራችን እንናገራለን፤ የተሳሳተዉንም እንቃወማለን" በሚሉ ትንታጎች፤ እንደ እስክንድር፤ ተመስገን፤ ርእዮት፤ አንዱ አለም፤ ዉብሸት፤ በቀለና በሌሎችም አርበኞች ትግል ወኔቢስነትና የፍርሃት ባህል ተሰብሯል።

ስለሻምበል ፍቅረስላሴ፤ መንግስቱ ሃይለማርያምስ ምን አለ? ብለን ብንጠይቅ ደግሞ ከታሪክ ማህደር የሚከተለዉን እናገኛለን። የኢሰፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ፖሊት ቢሮ 106ኛ ጉባኤ ላይ ነዉ። ቀኑ ህዳር 5 1989 ነዉ። መንግስቱ፤ በሻምበል ፍቅረስላሴ የተሰላቸ ይመስላል። ለስብሰባዉ እንዲህ ይላል "ፍቅረስላሴ ከስራዉ ብዙ ጊዜ ቀርቷል።

አንዳንድ ጊዜ በጤንነት ምክንያት መሆኑን እንገነዘባለን። ነገር ግን በተለሳለሰ መንገድ መነጋገር ማቆም አለብን። ጥቂቶቻችሁ ብቻ ናችሁ ከመካከላችሁ ከልባችሁ ስራ የምትሰሩት ወይም ስብሰባ ላይ የምትሳተፉት። ነገር ግን እንደፍቅረስላሴ አልምጥና ዝም ብሎ ተመልካች የለም። አንድ ቀንማ ስብሰባ እየተካሄደ በግሉ መጽሄት ያነብ ነበር። ጸረ አብዮተኛ፤ ወይም ወንጀለኛና አድመኛ አይደለም። ነገር ግን የተመዛዘነ (stable) ጭንቅላት የለዉም፡ አንዳንዴም ባለጌ ነዉ። በዚህና በሌሎችም የዲሲፕሊን ጉድለቶች ከፓርቲዉና ከስልጣኑ በክብር ተባሯል"። መንግስቱ በተጨማሪ ስለ ፍቅረስላሴ የግል የጤንነት ታሪክና ምርመራ የማያስፈልግ ብዙ ተናግሯል፤ እሱን እንተወዋለን።

ይህ ማስረጃ የተገኘዉ ከደርግ ጽህፈት ቤት ከተገኙ መዛግብት ሲሆን፤ የጽሁፎችን ምርምር አጠናቅቀዉ፤ "የኢትዮጵያ አብዮት" በተባለዉ በ 2009 እ.ኤ.አ. በታተመዉ የእንግሊዝኛ መጽሃፋቸዉ ገጽ 143 ላይ ያቀረቡት የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ናቸዉ።

ኣንዳንድ የደርግ አባላት፤ ለምሳሌ ሻለቃ እንዳለ ተሰማና ሻለቃ ካሳየ አራጋዉ፤ ደርግ ስህተት እንደሰራና አገሪቷን ከፍተኛ ዉርደት እንዳደረሰባት ከምርና ከልብ በሃዘኔታ ተናግረዋል። ሻምበል ፍቅረስላሴ ግን ዛሬም ከመንግስቱ ሃይለማርያም ጋር ሆነዉ የተበላሸ ታሪክን ለማሰማመር ደፋ ቀና የሚሉ ይመስላሉ። እነ ጀ/ል ተሾመ ተሰማ (ምጽዋ)፤ እነ ዶ/ር ተስፋየ ደበሳይ (አዲስ አበባ)፤ እነ ሻለቃ በቀለ ካሳ (አጋዴን) በጠላት ከመያዝና ከመማረክ ብለዉ በነዳድ የአገር ፍቅር የራሳቸዉን ህይወት ያጠፉላት አገር፤ ዛሬ እፍረት የማይሰማቸዉ መቀመቅ የከተቷት የቀድሞ መሪዎቿ (ዋነኛዉ ፈርጥጦ የጠፋ) ታሪክ ሊበርዙ የሚሞክሩባት አገር ስትሆን ታሳዝናለች።

ሻምበል ፍቅረስላሴ መጽሃፍ ዉስጥ እንደማንኛዉም መጽሃፍ አናሳ ግድፈቶች ይገኛሉ። የጎደሉና የተሳሳቱ የኢህአፓ አመራር ስሞች አሉ፤ የህዝብ ድርጅት ጽህፈት ቤት ምልምል የኢህ አፓን አባል ዮናስ አድማሱን ሳይሆን በስህተት የጠቀሱት ታላቅ ወንድሙን ዮሃንስን ነዉ፤ ወዘተ…

መጽሃፉ ዉስጥ በተለይ በጥሩ አተራረካቸዉ ትምህርት የሚሆን ስጋ ሜዳ እንዴት ወደ ታጠቅ የጦር ሰፈር እንደተለወጠና የሚሊሺያዉ ስልጠና እንዴት እንደታካሄደ ያቀረቡት ዝርዝር (እንደተለመደዉ ኢህአፓን በአሻጥረኛነት ያለማስረጃ ከመክሰሳቸዉ በስተቀር) ሊመሰገን የሚገባዉ ነዉ (ገጽ 365)። እንዲሁም በመጨረሻዉ ምእራፍ 19 የጠቀሷቸዉ ደርግ ያከናወናቸዉና ያቀዳቸዉ ልማቶች ዝርዝር ጠቃሚ ነዉ። በጦርነት ዉስጥ ሆኖ ደርግ ያከናወናቸዉ የልማት መስኮች ሊያስመሰግነዉ የሚገባ ርምጃ ነዉ። ዛሬ ልማታዊ መንግስት ነኝ የሚለዉ ኢህአዴግ የሚኩራራባቸዉ ብዙዎቹ ያኔ የተጀመሩ ወይም የታቀዱ እንደሆነ እንገነዘባለን። ሆኖም፤ አማርትያ ሴንን የመሳሰሉ የዉጭ የልማት ኢኮኖሚስቶችና ባገራችንም በርካታ ጠበብቶች ደግመዉ ደጋግመዉ የተናገሩትና የጻፉበት ልማት ከዴሞክራሲ ጋር ተጣምሮ ካልሄደ ዉጠቱ አመርቂ እንደማይሆን፤ የደርግ የሙት ታሪክ የንድፈ ሃሳቡን ትክክለኛነት ያሰምርልናል። ኢህአዴግንም ወጥሮ የያዘዉ ይህ ሃቅ ነዉ።

በሌላ በኩል ግን መጽሀፉ ለምን ስለደርግ የኤርትራ ጦርነቶች እንዳላወሳ፤ መንግስቱ ሃይለማርያም ስለገደላቸዉ ሲሳይ ሃብቴ፤ አጥናፉ አባተ፤ታዋቂ አዋጊ ጀነራሎች፤ በመንግስቱ ላይ ስለተደረገዉ የመንግስት ግልበጣ ሙከራና ያለ ርህራሄ የፈጃቸዉን ባለሙያ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ጉዳይ አለማካተቱና ወደፊትም እጽፋቸዋለሁ ባሏቸዉ መጽሃፍት ቦታ የሌላቸዉ አርእስት መሆናቸዉ ግር ያሰኛል።

እንደመደምደሚያ፤ ለወደፊት የታሪክ መጽሃፍ የሚጽፉ አፍቅሮተ ደርግ ያደረባቸዉ ጽሃፍት ሊያስተዉሏቸዉ የሚገቡ ነገሮች ከላይ በበቂ የተዘረዘሩ ይመስላል። በጭፍኑ ያለፈ አስቀያሚ ታሪክን ኢህ አፓን በመክሰስና በኢህ አፓ በመላከክ ብቻ ይሸፈናል ብሎ ማሰብ ቂልነት ነዉ። የሚያዋጣዉና ተአማኒነትን የሚፈጥረዉ፤ ስህተቶችን አምኖ፤ ለስህተቶች መነሻ ምክንያቶችን አመላክቶ፤ ሁሉም ትምህርት የሚያገኝበትን መንገድ ማመቻቸትና የነገዋን ኢትዮጵያ በጋራ መገንባት አማራጭ የሌለዉ ጉዳይ ነዉ።

ሰሎሞን ገ/ስ

ጥር 2006 አ.ም. 4